በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል ዘጠኝ

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

## ልጆች ወላጆቻቸውን ይውደዱ

- የቤተሰባዊ ፍቅርን ገጽታ መግለጣችንን ለማጠቃለል ልጆች ለወላጆቻቸው ሊኖራቸውን የሚገባውን ፍቅር አስመልክቶ ጥቂት ማብራሪያዎችን እንሰጣለን፡፡ ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸውን ግኑኝነት አስመልክቶ የምንጠይቃቸውም ጥያቄዎች አሉ፡፡
  - ከወላጆቻችሁ ጋር ያላችሁ ግኑኝነት ዘወትር መቀበልን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ መስጠትና መቀበል ከሚታይባቸው ግኑኝነቶች መካከል አንዱ ነው?
  - ወላጆቻችሁን ኋላ ቀር ወይስ ዘመናዊና ተገቢ አቅጣጫን ተከትለው የሚራመዱ አድርጋችሁ ታስባላችሁ? ምክራቸውን አክብራችሁ ትቀበላላችሁ ወይስ ንቃችሁ ትተውታላችሁ? ልምዳቸውንና ማስተዋላቸውንስ አምናችሁ ትቀበላላችሁ?
- ልጆች ከወላጆቻችሁ ጋር የሚኖራችሁ ግኑኝነት የሚከተሉት መገለጫዎች እንዲኖሩት ያስፈልጋል፡፡

## *ወላጆችን በማክበር መውደድ ይገባል*

- ሕይወታቸውን ለልጆቻቸው መሥዋዕትነት ላደረጉ ወላጆች ሊሰጥ የሚገባውን ክብር አስመልክቶ አምላካችን እግዚአብሔር ራሱ በጣቶቹ ‹‹አባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፡፡›› *ዘጸ 20፡12፡፡* በማለት ጽፎ ትእዛዝ ሰጥቶናል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

*ወላጆችን በማክበር ሊሆን ይገባል…*

- ይኸው ትእዛዝ በመምህራችን በቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ዳግመኛ አጽንኦት ተሰጥቶበታል፡፡ «መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት፡፡» *ኤፌ 6፡2-3፡፡*
- በነፍስ ጡርነትዋ ወራት፣ ከተወለድንም በኋላ በማሳደግ እጅግ የምትንገላታዋ እናት የሚገባትን ክብር አስመልክቶ ጌታችን በቃና ዘገሊላ የሠርግ ቤት የእናቱን የእመቤታችንን የአማላጅነት ጥያቄ ተቀብሎ መልስ በመስጠት ገልጦልናል፡፡ ‹‹ኢየሱስም፦ አንቺ (ሆይ) ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት፡፡›› *ዮሐ 2፡4፡፡*
- እግዚአብሔር ሥራን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለእናቱ ለእመቤታችን ስላለው ፍቅርና ክብር ውሃውን ወደ ወይን በመለወጥ የእናቱን ጥያቄ ተቀብሎ የመጀመሪያውን ተአምር አድርጓል፡፡ በዚህም ጌታችን የማስተማር ሥራውን እናቱን በማገልገል ለእናቱ በመታዘዝ ጀምሯል፡፡
- ሥራውንም ሲፈጽምም በመስቀል ተሰቅሎ ለእናቱ ለእመቤታችን ያለው ጥንቃቄና ክብካቤ ምን ያህል እንደሆነ እናቱን እመቤታችንን ይንከባከባትና በነፍሱም ትጠቅመው ዘንድ ‹‹እናትህ እነኋት፡፡›› *ዮሐ 19፡27፡፡* በማለት ለቅዱስ ዮሐንስ አደራ በመስጠት በተግባር አሳይቶናል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

***ወላጆችን በማክበር ሊሆን ይገባል…***

- ካረፈችም በኋላ ሥጋዋን በክብር በመውሰድ (በማሳረግ) ለዓለም ሁሉ አማላጅ በማድረግ በረከታችን ትሆን ዘንድ ሰጥቶናል፡፡
- እናትን ስለማክበር የምንመለከተው ሌላው ትምህርት የሚገኘው ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን እናቱ ልትጎበኘው በመጣች ጊዜ ከፈጸመው ድርጊት ነው፡፡ ‹‹ቤርሳቤህም የአዶንያስን ነገር ትነግረው ዘንድ ወደ ንጉሡ ወደ ሰሎሞን ገባች ንጉሡም ሊቀበላት ተነሣ እጅ ነሳት፣ ሳማትም፥ በዙፋኑም ተቀመጠ ለንጉሡም እናት ወንበር አስመጣላት፥ በቀኙም ተቀመጠች፡፡›› *ቀዳ ነገ 2፡19፡፡*
- ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር ስንነጻጸር ልጆች የሆንን ባለማወቃችንና ባለማስተዋላችን የምንገኘው የት ነው? ከሰሎሞን ባለጠግነትና ትሕትና አንጻር በባለጠግነታችን የምንገኝበት ደረጃስ የት ነው?
- ታናናሾችም ብንሆን እናታችንን በአክብሮት እንከባከባለን? ይህ ጉዳይ እናትን አስመልክቶ ሁላችንም የምንፈተሽበት ነው፡፡
- ፍጹም ጥበበኛ እንደሆነ የሚያስብ ቢኖር ከጥበበኛው ከሰሎምን ይማር በእናቱ ፊት በመስገድና እጅ በመንሳት አክብሮቱን ገልጧልና፡፡
- የተወደዳችሁ እህቶቼና ወንድሞቼ ወላጆቻችሁን ስለማክበር ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ? ከሆነ እንዴት?
- ወላጆቻችሁን ስለማክበር ጥንቃቄ የምታደርጉት ዝግ ባለ ድምጽ በአክብሮትና በትሕትና በማነጋገር፣ በተለያዩ በዓላት (በልደታቸው ቀን፣ በቤተ ክርስቲያናችን ዐበይት በዓላት…) ስጦታ በመስጠት ነውን?
- የምናከብራቸው በሥራና በእውነት ነውን? ጥልቅ ከሆነ ፍቅር የተነሳ በእነርሱ ፊትም ሆነ ከጀርባቸው ስለ ወላጆቻችን በጎ ነገሮችን በመናገር ክብራቸውን እንገልጣለን?

# ይቆየን።

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org